መልእክት አራት

## ለሕይወታዊ ግንኙነታቸው
## የአብያተ ክርስቲያናት ውስጠ-መሠረታዊ ኅብረት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ራእ. 22፡1፤ ሐዋ. 2፡42፤ 1 ቆሮ. 10፡16-18፤ 2 ቆሮ. 13፡14፤ ፊልጵ. 2፡1፤ 1 ዮሐ. 1፡3፣ 7

**I. የአብያተ ክርስቲያናትን ውስጠ-መሠረታዊ ኅብረት ማየትና ወደ ውስጡ መግባት ያስፈልገናል፦**

ሀ. ኅብረቱ በሕይወታዊዋ የክርስቶስ አካል ብልቶች ሁሉ ውስጥ፣ በኩልና መካከል ያለ የዘላለማዊው ሕይወት መፍሰስ ነው፤ ይህም በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ውስጥ ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን በሚወጣው የሕይወት ውኃ ፍሰት በስዕል ተብራርቶአል—ራእ. 22፡1።

ለ. ልክ በሰው አካል ውስጥ የደም ዝውውር እንዳለ ሁሉ፣ በክርስቶስ አካል ውስጥም አዲስ ኪዳን ኅብረት ብሎ የሚጠራው ዝውውር አለ—1 ዮሐ. 1፡3፣ 7።

ሐ. የክርስቶስ አካል ኅብረት፣ ያም በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለው ኅብረት፣ የሐዋርያት ኅብረት ነው—ሐዋ 2፡42፤ 1 ዮሐ. 1፡3፦

1. ኅብረት የሚመጣው ከትምህርት ነው፤ በተሳሳተ መንገድና ከሐዋርያት ትምህርት፣ ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትምህርት በተለየ የምናስተምር ከሆነ፣ ትምህርታችን ወገንተኛ፣ ከፋፋይ ኅብረትን ያፈራል—ሐዋ. 2፡42፤ 1 ጢሞ. 1፡3-6፤ 6፡3-4፤ 2 ቆሮ. 3፡8-9፤ 5፡18፦

   ሀ. ትምህርት ኅብረትን ይፈጥራል፣ ኅብረት ከትምህርት ይመጣል—1 ቆሮ. 4፡17፤ 1፡9፤ 10፡16።

   ለ. ዛሬ በጌታ ምለሳ ውስጥ፣ በሐዋርያት ትምህርት ሥርና በሐዋርያት ኅብረት ውስጥ ነን—ሐዋ. 2፡42።

2. በሐዋርያት ኅብረት ውስጥ ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ኅብረት ማድረግ የግል ፍላጎቶቻችንን ወደ ጎን ማድረግና ለእግዚአብሔር አላማ መከናወን ከሐዋርያትና ከሦስታንዱ አምላክ ጋር መጋጠም ነው—ፊልጵ. 4፡14፤ 2፡1፤ ሐዋ. 2፡42፤ 1 ዮሐ. 1፡3፤ 1 ቆሮ. 1፡9፤ 3፡6፣ 12።

መ. አንዱ መለኮታዊ ኅብረት የተሸመነ ኅብረት ነው፦ የእቻ ለእቻ የምናደርገው ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር ከምናደርገው ኅብረት ጋር ተሸምኗል፦

1. የሐዋርያት የመጀመሪያው ልምምድ ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የሚያደርጉት ኅብረት ነበር፣ ነገር ግን ሐዋርያት ዘላላማዊውን ሕይወት ለሌሎች ሲዘግቡ፣ እቻ ለእቻ የሚያደርጉትን የመለኮታዊውን ኅብረት ገጽታ ተለማመዱት—1 ዮሐ. 1፡2-3፤ ተዛ. ሐዋ 2፡42።

2. ከቅዱሳን ጋር የምናደርገው የእቻ ለእቻ ኅብረት ከጌታ ጋር ወዳለ ኅብረት ያመጣናል፤ ከዚያም ከጌታ ጋር ያለን ኅብረት ከቅዱሳን ጋር ወደ ምናደርገው የእቻ ለእቻ ኅብረት ያመጣናል፦

   ሀ. ወደ መለኮታዊው ኅብረት ገጽታ ውስጥ የምንገባው በመለኮታዊው መንፈስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ነው፤ ይህ የኅብረት ገጽታ እርሱን በመውደዳችን ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ያለንን ኅብረት ያመለክታል—2 ቆሮ. 13፡14፤ 1 ዮሐ. 1፡3፣ 6፤ ማር. 12፡30።

   ለ. እቻ ለእቻ ወደ ምናደርገው የመለኮታዊው ኅብረት ገጽታ ውስጥ የምንገባው በሰው መንፈስ ነው፤ ይህ የኅብረት ገጽታ እርስ በእርስ በመዋደዳችን በመንፈሳችን መንቀሳቀስ ያለንን የእርስ በእርስ ኅብረት ያመለክታል—ፊልጵ. 2፡1፤ ራእ. 1፡10፤ 1 ዮሐ. 1፡2-3፣ 7፤ 1 ቆሮ. 16፡18 ፤ ማር. 12፡31፤ ሮሜ 13፡8-10፤ ገላ. 5፡13-15።

3. በዚህ መለኮታዊ ኅብረት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሸመናል፤ ይህ መሸመን በሕይወት ለማደጋችንና ለመለወጣችን ወደ መንፈሳዊ ማንነታችን ውስጥ መለኮታዊውን ይዘት ለማምጣት የእግዚአብሔርና የሰው መዋሐድ ነው—ዘሌ. 2፡4-5።

ሠ. መለኮታዊው ኅብረት በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሁሉን ነገር ነው፦

1. የኤሌክትሪክ ፍሰት ኤሌክትሪክ ራሱ እንደሆነ ሁሉ፣ የመለኮታዊው ሕይወት ኅብረት፣ የመለኮታዊው ሕይወት ፍሰት ፣ መለኮታዊው ሕይወት ራሱ ነው።
2. ኅብረት ሲጠፋ (ሳይኖር ሲቀር)፣ እግዚአብሔርም አይኖርም፤ እግዚአብሔር የሚመጣው እንደ ኅብረት ነው—2 ቆሮ. 13፡14፣ ራእ. 22፡1።

**II. የአብያተ ክርስቲያናትን ሕይወታዊ ግንኙነት ማየትና ወደ ውስጡ መግባት ያስፈልገናል፤ ይህ የልዩና ብቸኛይቱ ቤተ ክርስቲያን (ከሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የተዋቀረችው አጽናፍ-ዓለማዊቷ ቤተ ክርስቲያን) ልዩና ብቸኛ**

**ግንኙነት ነው፤ በ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡28 “ቤተ ክርስቲያን” የሚለው ቤተ ክርስቲያንን በአጽናፍ-ዓለማዊ እና በአጥቢያዊ ገጽታዋ ያመለክታል፡-**

ሀ. ይህ ሕይወታዊ ግንኙነት ተግባራዊ ልምምድ ላይ የሚውለው ልዩና ብቸኛ እንዲሁም አጽናፍ-ዓለማዊ በሆነ መልኩ እንደ ልዩና-ብቸኛይቱ የክርስቶስ ሕይወታዊ አካል በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ነው—2 ቆሮ. 13፡14፤ 1 ዮሐ. 1፡3፣ 7።

ለ. አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አንድ ቤተ ክርስቲያን ናቸው፤ ሕይወታዊው ግንኙነታቸውም የተመሠረተው በመለኮታዊው ሕይወት ሕይወታዊ ኅብረት ላይ ነው፤ አንዷን አጽናፍ-ዓለማዊ የክርስቶስ አካል በሚያዋቅሩት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ድርጅት የለም፣ ነገር ግን የክርስቶስ አካል ኅብረት አለ—ፊልጵ. 1፡5፤ ተዛ. ሐዋ 9፡31።

ሐ. በአንድ አጥቢያ ያለች ቤተ ክርስቲያን በሌላ አጥቢያ ካለች ቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላት አይነት አመለካከት ሊኖራት አይገባም፤ የአብያተ ክርስቲያናት የተነጠለ፣ የራስ አገዛዝ ነጻነት ያለው ግንኙነት ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መልኩ የተሳሳተ ግንዛቤና ልዩ ትምህርት በእኛ መካከል ሲኖር ቆይቷል፤ ይህ የተሳሳተና ልዩ ትምህርት በክፍፍል ላይ ክፍፍልን ያመጣል።

መ. የጌታ ምለሳ ክርስቶስ በብዙ አጥቢያዎች ውስጥ እንደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የምትገለጥ አንድ አካል ብቻ አለችው በሚለው እውነት ላይ የተመሠረተ ነው፤ አንድ መንፈስ ስላለ፣ አንድ አካል ብቻ አለ፣ በአካሉ ውስጥም አንድ የሕይወት ዝወውር ብቻ አለ፤ ይህ ዝውውር በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለ ኅብረት የሆነ የክርስቶስ አካል ኅብረት ነው—ኤፌ. 1፡22-23፤ 4፡4-6፤ 1 ዮሐ. 1፡3፣ 7፤ ራእ. 1፡11።

ሠ. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የልዩና ብቸኛይቱ የክርስቶስ አካል ክፍል ናት፣ የአካሉ ኅብረት በአጽናፍ-ዓለም አንድ ነው፤ በመለኮታዊው ኅብረት ውስጥ መነጣጠል የለም—ቁ. 11፤ 2፡7፡-

1. የትኛውም ቤተ ክርስቲያን ወይም ቀጠና (region) ከአካሉ ኅብረት ራሱን ማግለል የለበትም፤ አንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቀጠና ራሱን ከክርስቶስ አካል ኅብረት የማግለሉ ውጤት ጨለማ፣ ግራ መጋባት፣ ክፍፍልና ሞት ነው።
2. ከአካሉ ኅብረት ራሳችንን ካገለልን፣ የጌታን እራት ለመካፈል የበቃን አንሆንም፣ ምክንያቱም በጌታ እራት በጠረጴዛው ላይ ያለው ቂጣ የሚያመለክተው መላውን የክርስቶስ አካል ስለሆነ ነው—1 ቆሮ. 10፡16-17፤ 11፡25-28።

**III. መለኮታዊው ኅብረት በመንፈስ አንድነት በክርስቶስ አካል ውስጥ የመኖር እውነታ ነው—1፡9፤ 10፡16-18፤ 12፡12-13፣ 27፤ ሐዋ. 2፡42፤ ኤፌ. 4፡3፡-**

ሀ. መለኮታዊው ኅብረት ያገጣጥመናል፤ ያም ማለት፣ ያስተካክለናል፣ በኅብር ያደርገናል፣ ሚዛን ያስይዘናል እና ወደ አንድ አካል በአንድ ላይ ያዋሕደናል—1 ቆሮ. 10፡17፤ 12፡24-25፡-

1. በአንድ ላይ መገጣጠም በመስቀሉ በኩል መሄድና ስለ ክርስቶስ አካል ስንል ወደ ሌሎች ውስጥ ክርስቶስን ለማደል ሁሉን ነገር በመንፈስ ማድረግ ነው—ተዛ. 2ዜና. 1፤10።
2. ከእኛ ጋር ከሚቀናጁት ቅዱሳን ጋር ኅብረት ሳናደርግ የትኛውንም ነገር ማድረግ የለብንም፤ ኅብረት የሆነን ነገር ልናደርግ ስንል ቆም እንድንል ይጠይቃል—ተዛ. ሕዝ. 1፡11-14።

ለ. በመለኮታዊው ኅብረት ውስጥ በመገደብ፣ የክርስቶስ አካል በአንድነት ትጠበቃለች፣ የአገልግሎቱም ሥራ ወደ ፊት መሄዱን ይቀጥላል፤ ሁሉንም ነገር ሕያው የሚያደርገው ኅብረት ነው—ኤፌ. 4፡11-12፤ ተዛ. ሕዝ. 47፡9።

ሐ. አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ወደ ክርስቶስ አካል ኅብረት ውስጥ ለማምጣት ሐዋርያውን መምሰል እና ቅዱሳንን ሁሉ ወደ መላው የክርስቶስ አካል የመገጣጠም ሕይወት ውስጥ ለማምጣት የሐዋርያውን ዱካ መከተል ያስፈልገናል—ሮሜ. 14፡3፤ 15፡7-9፣ 25-33፤ ምዕ. 16።

መ. የክርስቶስ አካል ኅብረትና መገጣጠም እውነታ ሊኖረን ያስፈልጋል፤ አለበለዚያ፣ ምንም እንኳን ወደ ሆነ ግብ ለመድረስ የምንተጋ እና ምንም ያህል ቀለል ያልንና ትሁት ብንሆንም፣ ይፍጠን ወይ ይዘግይ እንጂ በመካከላችን ችግሮች፣ ክፍፍሎችም እንኳ ሳይቀሩ ይኖራሉ።

ሠ. የመገጣጠም አላማ ሁላችንንም ወደ የክርስቶስ አካል እውነታ ውስጥ ለማምጣት ነው፤ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን እንደ ውድ ነገር የምንወስወደው ለአላማ ነው—ወደ ክርስቶስ አካል እውነታ ውስጥ እንዲያመጣን የክንዋኔ ሂደት በሆኑት በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መሆን ያስፈልገናል።

*© 2021 Living Stream Ministry*